17ኛ ዓመት ቁጥር 24
17th Year No 24

ባሕር ዳር የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም
Bahir Dar February 19,2013

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር
Unit price …….

## ማውጫ

**አዋጅ ቁጥር 200/2005 ዓ/ም**

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ**

## Contents

**Proclamation No.200 /2012**

**The ANRS Revised Mass Media Agency Establishment Proclamation Amendment Proclamation**

## አዋጅ ቁጥር 200/2005 ዓ/ም

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የክልሉ ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

በሥራ ላይ ያለው የአማራ ክልል ብዙሃን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 88/1995 ዓ/ም በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆን ዘንድ የድርጅቱ ሙያተኞችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን ሥርዓትና የፋይናንስ አስተዳደሩን የሚመለከቱ ድንጋጌዎቹን ማሻሻልና ይበልጥ ግልፅ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## Proclamation No.200 /2012

**A Proclamation Issued to Amend the Revised Mass Media Agency Establishment Proclamation of the Amhara National Regional State**

WHEREAS, it has been found necessary to improve and make more clear the provisions concerned to the administration procedure of the agency's professionals and supporting staff and finance administration of the Amhara Region mass media agency establishment proclamation No 88/2003, that is in effect to be implemented successfully;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የአማራ ክልል ብዙሀን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 200/2005 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

## 2. <u>ማሻሻያ</u>

የተሻሻለው የአማራ ክልል ብዙሀን መገናኛ ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 88/1995 ዓ/ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል፡፡

ሀ/ የአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ /1/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሐ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ ቁጥር /ሐ/ ተተክቷል፡፡

/ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ሥራ አስኪያጆች፡፡

ለ/ የአዋጁ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀጽ /7/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /7/ ተተክቷል፡፡

/7/ የተቋሙን የሥራ ባህሪ ባገናዘበና ከክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በድርጅቱ ሥራ አመራር ተጠንተው የሚቀርቡለትን የድርጅቱን ጋዜጠኞችና የፕሮዳክሽንና የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዲሁም ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ቅጥር፣የደመወዝ ስኬል፣አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች ይወስናል፤ እንደ አስፈላጊነቱ ያሻሽላል፡፡

NOW, THEREFORE, the council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under Article 49 sub-articles 3/1/ of the Revised constitution of the National Region, here by issues this proclamation.

## 1. <u>Short Title</u>

This proclamation may be cited as " a revised mass media agency of the Amhara Region establishment proclamation amendment proclamation No 200/2012''

## 2. <u>Amendment</u>

The revised Amhara Region mass media agency establishment proclamation No.88/2003 is amended as follows by this proclamation:

A/ Alphabet /c/ of sub –article /1/ of Article 6 of the proclamation is deleted and replaced by the new alphabet /c/.

C/ Deputy managers, as may be necessary.

B/ sub- article /7/ of Article 9 of the proclamation is deleted and replaced by the new sub-article /7/.

/7/Recognizing the agency's work situation and in harmony with the region civil service laws, regulations and derectives, decide the agency's journalists,production and technic professionals, as well as supporting staff recruitment, salary scale, perdiem and other fringe benefits that has been presented studying by the agency's management .

ሐ/ በአዋጁ አንቀጽ 9 ሥር ከንዑስ አንቀጽ /7/ ቀጥሎ የሚከተሉት አዳዲስ ንዑስ አንቀጾች 8 እና 9 ድንጋጌዎች የገቡ ሲሆን ቀሪዎቹ ድንጋጌዎች በዚሁ መሠረት ወደፊት ተሸጋሽገዋል፡፡

/8/የጋዜጠኞች፣ የፕሮዳክሽንና የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዲሁም ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ማንዋል ረቂቅ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብለት ያደርጋል፤ይህንኑ መርምሮ ያፀድቃል፣በሥራ ላይ እንዲውልም መመሪያ ይሰጣል፤

/9/በክልሉ የሚሠራባቸውን የፋይናንስ፣የግዥና የንብረት አስተዳደር ህጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በማድረግ ተዘጋጅተው የሚቀርቡለትንና ከድርጅቱ የሥራ ባህሪ ጋር የተጣጣሙ መሰል የግዥ፣ ፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ማንዋሎችን መርምሮ ያፀድቃል፣ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

መ/ የአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ /3/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሐ/ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ ቁጥር /ሐ/ ተተክቷል፡፡

/ሐ/ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የድርጅቱን ጋዜጠኞች፣የፕሮዳክሽንና የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዲሁም ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ያሰናብታል፡፡

/ሠ/ ከአዋጁ አንቀጽ 12 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ 13 የተጨመረ ሲሆን በዚሁ አዲስ አንቀጽ መግባት ምክንያት ተከታዩቹ አንቀጾች ወደፊት ተሸጋሽገዋል፡፡

C/ Next to sub-article/7/ of Article 9 of the proclamation, the following new sub- articles 8 and 9 provisions are included; the remaining provisions are arranged forward.

/8/ cause making and preparing the administration manual draft, of journalists, production and technic professionals, as well as supporting staff, be submitted; approving this by examining and giving direction to be in effect;

/9/ pursuant to finance, procurement and property administration laws, regulations and directives that are applicable in the region, approve by examining similar finance and property administration manuals which are in harmony with the agency's work situation that are submitted by preparing; cause it to be in effect.

D/ Alphabet/c/ of sub-article /3/ of Article 11 of the proclamation is deleted and replaced by the following new alphabet/c/.

/c/pursuant to directives which shall be issued by the board; recruit, administer and dismiss the agency's journalists, production and technic professionals, as well as supporting staff.

E/ Next to Article 12 of the proclamation, the following new Article 13 is included; pursuant to the entrance of this new Article, the subsequent Articles are arranged forward.

/13/ ስለቅሬታ አቀራረብና አወሳሰን

1. የድርጅቱ ጋዜጠኞች፣ የፕሮዳክሽንና የቴክኒክ ባለሙያዎች እንዲሁም ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በዚህ አዋጅ መሠረት የሚያነሷቸው ቅሬታዎች ለቦርዱ ቀርበው ውሣኔ ያገኛሉ፡፡

2. ቦርዱ በፍሬ ነገር ክርክር የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤ ሆኖም ዉሳኔዉ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ ያመነ ወገን ቦርዱ ዉሳኔ በተሰጠ በ30 ቀናት ዉስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

ባሕር ዳር

የካቲት 12 ቀን 2005 ዓ.ም

አያሌዉ ጎበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዘዳንት



/13/ Grievance Submission and Decision Making

1. Pursuant to this proclamation, the raising grievances, of the agency’s journalists’ production and techinc professionals, as well as supporting staff, shall get decision submitted to the board.

2. The decision of the board on question of facts shall be tried; provided; however, that any one of the parties May appeal to the regional supreme court on question of law within 30 days from the late of the desion of the board.

## 3. <u>Effective Date</u>

This proclamation shall comeinto force as of the date of its publication in the Zikre-Hig Gazettee of the Rgional State

Done at Bahir Dar,

This 19 th day of February 2013

Ayalew Gobezie

President of the Amhara National Region